# በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ለሚቀጠሩ የውጭ አገር ዜጎች አዲስ የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

## ሀ. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

1. የቀጣሪ ድርጅት የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም፤ 4 ኮፒ
2. የድጋፍ ደብዳቤ ፤
   - ፕሮጀክት ሥራን ለመተግበር ለሚመጡ ባለሙያዎች ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፤
   - ለድርጅቱ ተጠሪና በከፍተኛ የማኔጅመንት ቦታ ላይ ለሚሠማሩ ከፍትህ ሚኒስቴር፤
   - በኃይማኖት ሥራ ላይ ለሚሠማሩ ከፍትህ ሚኒስቴር፤
   - በጤናና በትምህርት ዘርፍ የሚሠማራ ከሆነ ከጤናና ከትምህርት ሚኒስቴር፤
   - ለማህበራት እንደ አግባቡ ከሚመለከተው መ/ቤት ድጋፍ /ማስረጃ
   - በተገቢው ሙያ የትምህርት ማስረጃ
3. የፓስፖርት ፎቶ ኮፒ ፤
4. አራት የፓስፖርት መጠን ያላቸው / 3X4/ የቅርብ ጊዜ ተመሳሳይ ፎቶግራፍ፤

5. ክፍያ 600.00 / ስድስት መቶ ብር ብቻ

<u>መንግሥታዊ ድርጅቶች</u>

1. የቀጣሪ ድርጅቱ የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም፤ 4ኮፒ
2. ፕሮጀክቱን በቅርብ ከሚያስፈጽም የመንግሥት ድርጅት በላይ ኃላፊ የተፈረመ የድጋፍ ደብዳቤ ፤
3. የፓስፖርት ፎቶ ኮፒ፤.........
4. የፓስፖርት መጠን ያላቸው / 3X4/ የቅርብ ተመሳሳይ ፎቶግራፍ ብዛት 4
5. በጤናና በትምህርት ዘርፍ የሚሠማራ ከሆነ ከጤናና ከትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍ / ማስረጃ ፤
6. በተገቢው ሙያ የትምህርት ማስረጃ ፤
7. ክፍያ 600.00 / ስድስት መቶ ብር ብቻ/

ሐ. <u>ግል ድርጅት</u>

1. የቀጣሪ ድርጅት የሥራ ፈቀድ ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም፤ 4 ኮፒ
2. ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን / ቢሮ የተሰጠ የኢንቨስትመንት ሠራተፊኬት ወይንም የንግድ ፈቃድ፤ ወይም የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ በድርጅቱ ስም የተሰጠውን ንግድ ፈቃድ ማስረጃ፤
3. የፓስፖርት ፎቶ ኮፒ፤
4. እንደአግባቡ ከሚመለከተው መ/ቤቱ የድጋፍ ደብዳቤ / ማስረጃ
5. አራት የፓስፖርት መጠን ያላቸው /3X4/ የቅርብ ጊዜ ተመሳሳይ ፎቶግራፍ ፤
6. በተገቢው ሙያ የትምህርት ማስረጃ
7. ክፍያ 600.00 / ስድስት መቶ ብር ብቻ/

<u>ማ ሳ ሰ ቢ ያ</u>

ለሁሉም ድርጅቶች የውጭ አገር ዜጋው ቀደም ሲል ሌላ ድርጅት ውስጥ ይሠራ ከነበረ ክሊራንስ ማቅረብ ይኖርበታል።

## *በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የፈቃድ እደሳት ለማድረግ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች*

1. ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት የዕድሳት ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ ፤
2. ከወንጀል ድርጊቶች ነፃ ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ ፤
3. የወኪሉን የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማስረጃ ማቅረብ ፤
4. የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ ለመፈፀም ብር 200 / ሁለት መቶ / የሚተካ ከሆነ ብር 250 ፤
5. የዘመኑ የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትና ግብር የተከፈለ ስለመሆኑ ማስረጃ የማቅረብ እና
6. ለሥራ ወደ ውጭ አገር ስላሰማራቸውና ስለተመለሱ ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ ማቅረብ ፤

# በውጭ አገር የሥራ ስምሪት ላይ ለመሳተፍ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የቀረበ የጥያቄ ማመልከቻ ፤
2. በኤጀንሲነት ሥራ ላይ ለመስራት የሚያስችለው የንግድ ምዝገባ፤
3. በግል በሽርክና በአክሲዮን ወይም ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር የሚቋቋም ከሆነ አመልካቹም ሆነ ሰራተኞቹ በሕገወጥ የሥራና ሠራተኛ ማገናኘትና የሰዎች ዝውውር የተቀጣ / የተቀጡ/ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ ፤
4. የአደረጃጀት መዋቅርና የሠራተኞች ስም ዝርዝር ፤
5. የአመልካቹ የወኪሉ የሥራና የመኖሪያ አድራሻ እንዲሁም የባለቤትነት ማረጋገጫ ፣ ወይም የኪራይ ውል ፤
6. ለቢሮ ሥራ ክትትል ለማድረግ እና የሙያ ምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ባሙያዎች መመደቡን ማስረጃ ማቅረብ ፤
7. ሠራተኞችን በሚልኩበት አገር ወኪል የሰየመ መሆኑንና ወኪሉ በሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ፤

8. ሠራተኛን በሚልኩበት አገር የተሟላ ቢሮና ጊዜያዊ የምግብና የመጠለያ አገልግሎት ስለመኖሩ በኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንስላ ጽ/ቤት/ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ፤
9. የተሟላ ቢሮና የቅድመ ቅጥርን ስምሪት የምክር አገልግሎት መስጫ መዘጋጀቱ በመ/ቤቱ ኢንስፔክተር ሲረጋገጥ ፤
10. ለሠራተኛ መብት ማስከበሪያ የሚውል የሚከተለውን ገንዘብ መጠን ሃምሣ በመቶ / 5% / ከታወቀ የገንዘብ ድርጅት የተረጋገጠ የማይሻር የዋስትና ወረቀት ማስቀመጥ፤

ሀ/ እስከ 500 ለሚደርሱ ሠራተኞች 30000 / ሰላሳ ሺ/ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር ፤

ለ/ ከ 501- እስከ 1000 ለሚደርሱ ሠራተኞች 40 000/ አርባ ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር፤

ሐ/ ከ1000 በላይ ለሚሆኑ ሠራተኞች 50.000/ አምሳ ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር ፤

11. የፈቃድ ክፍያ መክፈል ብር 300/ ሶስት መቶ ብር/ ፤